# ግላዊነት እና እርስዎ

ተሳታፊዎች ምን አይነት መረጃ “ግላዊ” መሆን እንዳለበት ይለያሉ፣ ማህበራዊ ሚድያ ላይ ግላዊነትን እንዴት እንደሚያበጁ፣ እንዲሁም ቅንብሮቻቸውን (ለምሳሌ፣ የሆነ ይዘት ለምን "ጓደኞች ብቻ" ወይንም "ይፋዊ" ቅንብር ላይ እንደተደረገ) የሚመለከት ውሳኔ አሰጣጥ እንዴት እንደሚያስኬዱት ያብራራሉ። ተሳታፊዎች ምን አይነት መረጃ “ግላዊ” መሆን እንዳለበት ይለያሉ፣ ማህበራዊ ሚድያ ላይ ግላዊነትን እንዴት እንደሚያበጁ፣ እንዲሁም ቅንብሮቻቸውን (ለምሳሌ፣ የሆነ ይዘት ለምን "ጓደኞች ብቻ" ወይንም "ይፋዊ" ቅንብር ላይ እንደተደረገ) የሚመለከት ውሳኔ አሰጣጥ እንዴት እንደሚያስኬዱት ያብራራሉ።

## ማቴርያሎች

የግምት ጌም የሚታደል ጽሑፍ

# የግምት ጌም

## ክፍል 1

**የክላስ መስተጋብር**

የግምት ጌም የሚታደል ጽሑፉን ያድሉ እና እያንዳንዱ ተሳታፊ እንዲሞላው ይጠይቁ። ተሳታፊዎች አራት የሚያጋሩዋቸው ንኡስ መረጃዎችን እንዲመርጡ ይጠይቁዋቸው እና እነሱ የጻፉት መረጃ ለጠቅላላ ቡድኑ እንደሚያጋሩት ያሳውቁዋቸው። ሁለተኛውን ወረቀት እንዲያቆዩት ይዘዙዋቸው።

መልመጃውን ለማጠናቀቅ ለተሳታፊዎች 10 ደቂቃ ይስጧቸው። ከዛ በኋላ፣ የሚታደሉ ጽሑፎችን ይሰብስቡዋቸው።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

አሁን የሚታደል ጽሑፉ ላይ ከሚገኙት መረጃዎች ውስጥ የተወሰኑትን ላነብላቹ ነው። እያንዳንዱን የሚታደል ጽሑፍ የትኛው ተሳታፊ እንደሞላው ግምትዎ ለመጻፍ የግምት ክፍሉን ይጠቀሙ።

**የክላስ መስተጋብር**

የሚታደሉት ጽሑፎች ካነበቡ በሗላ፣ ቡድኑን ውይይት ላይ ያስገቡት።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

*ለማንም ሰው ያላጋሩዋቸው መረጃዎች ነበሩ? የትኞቹ ናቸው? ለምን?*

*የትኛውን ነገር ማጋራት እንዳለበት ተመሳሳይ ውሳኔ የወሰደ ሰው ነበር? ለምን / ለምን አልሆነም?*

*በሚያጋሩት ሰው ላይ ተመስርቶ፣ የዚህን አይነት መረጃ ከዚህ በላይ ወይም በታች ሊያጋሩ የሚችሉበት ምክንያት ምን ይሆን ነበር? መቼ ነው የሚያጋሩት?*

*እያንዳንዱ መረጃ ከጻፈው / ከተናገረው ሰው ጋር ማገናኘት ምን ያህል ቀላል ነበር?*

*የሆነ ምላሽ ሳይታሰብ ከተጨባጩ ምላሽ የተለየ መልእክት ያስተላለፈባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ (ለምሳሌ፣ አንድ ሰው የሚወደው ምግብ በመግለጹ ምክንያት ይህ ሰው ከየትኛው ባህል(ሎች) እንደሚዛመድ ምልክት እንደመስጠት ተደርጎ የተወሰደበት አጋጣሚ)?*

*የግምት ጌም አካል አድርገው የጻፉት መረጃ ለሰፊው አለም ቢያጋሩ ሌሎች ሰዎች ስለእርስዎ ምን ግምት የሚይዙ ይመስሎታል?*

## ክፍል 2

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

ግላዊነት ማለት ሌሎች ሰዎች ስለ እርስዎ የሚያውቁትን ነገር የመቆጥጣጠር ችሎታ ማለት ነው። ይህን ስለ እርስዎ የተወሰኑ ነገሮችን በመናገር ይፈጽሙታል (ለምሳሌ ለሌሎች ሰዎች አድራሻዎን ወይም ዘና ለማለት ምን ማድረግ እንደሚያስደስትዎ) ወይም ነገሮችን ሌሎች ሰዎች ባሉበት በማድረግ (ለምሳሌ ከጓደኞች ጋር ወደ መደብር መሄድ እና የሚፈልጓቸውን ነገሮች መምረጥ)። ከሌሎች ሰዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ቢሆኑም ወይም ከእነርሱ ጋር በመስመር ላይ የሚያወሩም ቢሆን ግላዊነት አስፈላጊ ነው።

ግላዊነት በራስዎ ውሳኔ የሚመሰረት ነው። ግላዊነት ለእርስዎ ወይም ለቤተሰብዎ የሚሰጠው ትርጉም በዚህ ቡድን ውስጥ ላሉ ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከሚሰጠው ትርጉም የተለየ ሊሆን ይችላል። እኛ የግል ነው ብለን ዋጋ የምንሰጠውን ነገርን እና በመስመር ላይ የሚኖረን ጠባይ እንዴት ግላዊነታችን ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው የምናውቅ ከሆነ፣ ምን አይነት ግላዊነት እንደምንፈልግ የተሻሉ ምርጫዎችን ለመውሰድ እንችላለን።

ግላዊነት በሚጋራው መረጃ አይነት እና በሚጋራው አካል ላይ ጭምር በመመስረት ይቀያየራል።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

ለምሳሌ፣ የቤት አድራሻዎ ለሚከተሉት ሰዎች ሊያጋሩ ይችላሉ:

1. የእርስዎ ወላጆች / ተንከባካቢዎች ወይንም ሌሎች ቤተሰብዎ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ አዋቂዎች?
2. የእርስዎ ጓደኞች?
3. አስተማሪዎ?
4. በሚገባ የማያውቁት እንግዳ / ሰው?
5. የጓደኛ ጓደኛ?
6. ድርጅት ወይንም ኩባንያ?

## *ማጠቃለያ*

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

*መረጃ በኦንላይን ሲያጋሩ፣ መረጃው ማን ሊያየው እንደሚችል እንዲሁም እርስዎ ወይንም መረጃው እየተጋራበት ያለው ሰው መረጃው ለተወሰኑ ታዳሚዎች መጋራቱ እንደማያስከፋው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።*

*እንዳንድ መረጃ ለማይገባቸው ሰዎች ከተጋራ በሚቀጥለው ጊዜ መጥፎ ችግር ሊያስከትል ይችላል። እንግዳ / በሚገባ የማያውቁት ሰው እርስዎ የሚኖሩበት ቦታ የሚያውቅ ከሆነ፣ ወደ እርስዎ ቤት ሊመጡ ይችላሉ፣ ይህ ደግሞ ለደህነንት ጥሩ አይደለም። ይህ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ብዙም የሚያጋጥም ባይሆንም፣ ድንገት ብያጋጥም ጉዳቱ (እንዲሁም ሊያጋጥም የሚችል ጉዳት) ከባድ ሊሆን ይችላል። የእርስዎን ደህንነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ የግላዊነት አማራጮችን ለመረዳት፣ መረጃውን የመጋራት ጉዳቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት አለብዎ።*

# አለመናበብ

## ውይይት

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

በጽሑፍ መልእክቶች ምን እንደተባባልን፣ እንዴት እንደተናገርን፣ እና በአካል ከመነጋገር ምን እንደሚለየው እንነጋገር።

### ተማሪዎችዎን ይጠይቁ

አንድ ነገር በጽሑፍ መግለጽ በአካል ከመናገር የሚለይበት ምክንያት ምንድነው?

1. የሰውየውን ተግባረ-መልስ ማየት ካልቻሉ፣ እርስዎ ስለተናገሩት ነገር ምን እንደተሰማቸው ማወቅ አይችሉም። ካለማወቅ የአንድን ሰው ስሜት ሊጎዱ ይችላሉ።

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

አንድን ሰው በግንባር ተገናኝተው ሲያወሩት፣ የእነሱን ተግባረ- መልስ፣ አካላዊ ቋንቋን እና የድምጻቸው ድምጸትን ጨምሮ በቀጥታ መታዘብ ይችላሉ። በመስመር ላይ ሲወራ ግን የተወሰነው የዚህ አውድ ክፍል ይታጣል።

ሆኖም፣ መስመር ላይ ሌሎች ለተግባቦት የሚጠቅሙ የአውዳዊ መረጃ አይነቶችን ማግኘት ይችላሉ (ለምሳሌ፣ መድረኮች (platforms) ከመረጃ አተረጓጎም ጋር በተያየዘ የተሻለ ስሜት የሚፈጥሩብዎ ልምዶች ሊሰጠዎት ይችላሉ)።

### ተማሪዎችዎን ይጠይቁ

የተወሰኑ አውዳዊ ረድፎችን ቢያጡ፣ (ለምሳሌ፣ የምልክት ቋንቋ፣ የድምጽ ድምጸት)፣ ይህ እንዴት ሌሎች ተቀባዮች በተሳሳተ መንገድ ሊረዱዋቸው ወደ ሚችሉዋቸው ጽሑፎችዎ ወይንም የመስመር ላይ መልእክቶችዎ ሊያመራ ይችላል (ለምሳሌ፣ አንድ ቀልድ በተሳሳተ መንገድ ተተርጉሞ የሌላ ሰው ስሜት ሊጎዳ ይችላል)?

በግንባር ተገናኝተው የሚያወሩት ሰው በተሳሳተ መንገድ ከተረዳዎት፣ ብዥታውን ለማጥራት ምን ማድረግ ይኖርብዎታል (ለምሳሌ፣ ይቅርታ ሊጠይቁ ወይንም ማለት የፈለጉት ነገር እንደገና ያብራራሉ)? ይህ እንዴት ከጽሑፍ መልእክት የተለየ ይሆናል (ለምሳሌ፣ ከባድ ወይንም ቀላል)?

# ማነው የእርስዎ ታዳሚ?

## ክፍል 1

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

*መስመር ላይ ከምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎቻችን የውሂብ ምልክቶች መተዋችን የማይቀር ቢሆንም፣ ግላዊነታችን የምንቆጣጠርባቸው እና የመስመር ላይ ክብራችንን የምናስተዳድርባቸው መንገዶች አሉን። በማህበራዊ ሚድያ አውድ፣ የለጠፍነውን ማየት ያለበት ማን እንደሆነ ለመምረጥ የሚያስችሉን ቅንብሮች ከፕላትፎርሞቹ ላይ ተካትተዋል። ምንም እንኳ እነ እነዚህን ቅንብሮች ማስተካከል ትንታኔ— የሜታዳታ ትንታኔን ጨምሮ — ለምሳሌ፣ የሶስተኛ አካል ቡድኖች ትንታኔዎችን የሚገድብ ባይሆንም (ለምሳሌ፣ አስተዋዋቂዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ወይንም ኩባንያዎች) እንዲሁም የፕላትፎርሞቹ ትንታኔዎች የማይገድብ ቢሆንም፣ ሌሎች የማህበራዊ ሚድያ ተጠቃሚዎች ምን ማየት እንዳለባቸው ወይንም የመረጃ ኩባንያዎች ወይንም አስተዋዋቂዎች ማግኘት ያለባቸው መረጃ ላይ ገደብ ይጥላል።*

*ጥያቄ ለሚያነሱ ሰዎች፣ ሜታዳታ በመሰረቱ ውሂብን የሚመለከት ውሂብ ነው። ሜታዳታ ወደ ማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርም በየትኛው ሰአት እንደገቡ፣ ከየት ቦታ እንደገቡ፣ እንዲሁም የኦንላይን ግንኙነቶችዎ የሚጨምር መረጃ እና ሌሎችን ሊያጠቃልል ይችላል።*

*የግላዊነት ቅንብሮች እንደየ ማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርሙ የተለያየ ምስል ቢኖራቸውም፣ ጥቅማቸው ግን ታዳሚያችንን እንድንመርጥ ማስቻል ነው። ለምሳሌ፣ ቅንብሮቹ ልጥፎቻችንን ሙሉበሙሉ ይፋዊ እንዲሆኑ፣ ለጓደኞቻችን ጓደኞች ብቻ ግልጽ እንዲሆኑ፣ ለጓደኞቻችን ብቻ እንዲታዩ፣ እና፣ አንዳንድጊዜ፣ ለተመረጡ ግለሰቦች ብቻ እንዲታዩ ለማድረግ ያስችሉናል። እነዚህ ቅንብሮች እንደ የመገኛ ቦታ ውሂብ እና የማጋራት ፈቃድ የመሳሰሉ ሌሎች የትግበራ አይነቶችንም ሊነኩ ይችላሉ። በአብዛኞቹ አገልግሎቶች አማራጮች / ቅንብሮች ላይ ገብቶ ጥቂት ለውጦች በማድረግ ኩኪዎች፣ የታሰቡ ማስታወቂያዎች፣ እና የፍሊጋ ማጠናቀቆችን ማሰናከል ይቻላል። በተጨማሪም እርስዎ በድረገጾች (ለምሳሌ፣ ከኤሌክትሮኒክ ፍሮንተይር ፋውንዴሽን የተገኘው "አትመዝግብ" የግላዊነት ባጅር) መካከል በሚናኙበት ጊዜ የግላዊነት ጥበቃዎ ሊያጠናክሩ የሚችሉ የድር-አሳሽ ተጨማሪዎች እና ሌሎች ዲጂታል አገልግሎቶች አሉ።*

## ክፍል 2

**የከላስ መስተጋብር** *ተሳታፊዎችን በጥንድ ያደራጁ።* ***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

*አንድ ደቂቃ ወስደው መለያ የያዙባቸው እያንዳንዳቸው የማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርሞችን ያስቡ።*

በእያንዳንዳቸው እነዚህ የማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርሞች ላይ የእርስዎ የግላዊነት ቅንብሮች አሁን በምን ሁኔታ እንደሚገኙ ያውቃሉ?

## የቡድን እንቅስቃሴ

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

*ቅንብሮቹ የሚሰጡን አቅሞችን እንፈትሽ እንዲሁም የትኞቹ እጅግ ተገቢ እንደሆኑ፣ በምን አይነት ሁኔታ፣ እና በምን አይነት ፕላትፎርሞች እንደሚሰሩ እንይ።*

*ወደሚጠቀሙበት ማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርም በግል ይሂዱ እና የግላዊነት ቅንብሮችዎ ይመልከቱ። ሁልጊዜ፣ የግላዊነት ቅንብሮች በመለያ ቅንብሮችዎ ስር ይገኛሉ፣ አንዳንድ ፕላትፎርሞች ደግሞ ግላዊነትዎ የሚፈትሹባቸው ልዩ ማግበሪያዎችን ጭምር አካትተዋል።*

የግላዊነት ቅንብሮችዎ ከመረመሩ በኋላ፣ እነዚህን ቅንብሮች በተመለከተ አጋርዎን ያናግሩ። ለምንድነው እያንዳንዶቹ የግላዊነት ቅንብሮቻችሁን እንደሱ ያደረጋቹዋቸው? የግላዊነት ቅንብሮች አንዳንድ ጊዜ አውዳዊ ናቸው (ለምሳሌ፣ የሆኑ ቅንብሮች በአንድ ሁኔታ ተገቢ ሲሆኑ በሌላ ሁኔታ ግን አስፈላጊ አይደሉም)? ቅንብሮችዎ ቀይረው ያውቃሉ? በየስንት ጊዜው ይቀይሩዋቸዋል እንዲሁም ለምንድነው የሚቀይሩዋቸው?

ፕላትፎርሙ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰዎች መረጃ ከማጋራት ጋር ለተያያዙ የግላዊነት ቅንብሮች፣ እንዲሁም ፕላትፎርሙ ራሱ እና ማናቸውም ተዛማጅ ሶስተኛ አካላት (እንደ አስተዋዋቂዎች) ምን ያህል ውሂብ ሊቀበሉ እንደሚችሉ የሚያመላክቱት ላይ ትኩረትዎን ይጣሉ። ሁሉም ዲጂታል ግላዊነትዎ ከመቆጣጠር አንጻር ጠቃሚ አካላት ናቸው — ለእንግዶች / በደምብ ለማያውቋቸው ሰዎች፣ ጓደኞች፣ ቤተሰብ፣ እና ኩባንያዎች።

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ቁጥር ተደራጅተው እንዲወያዩ 5 ደቂቃ ይስጡዋቸው እና በመቀጠል ሁሉንም ወደ አንድ ቡድን በማምጣት የሚከተሉት ጥያቄዎችን ተጠቅመው እንዲወያዩ ያድርጉ።

## ውይይት

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

አጠቃላይ መለያዎ ይፋዊ፣ ግላዊ፣ ወይንስ ሌላ የግላዊነት ሁኔታ ላይ

ነው ያለው? እዚህ ቅንብር ላይ እንዲሆን እንዴት ወሰኑ?

አሁን የግላዊነት ቅንብርዎ እርስዎ እንደሚፈልጉት ነው ያለው?

በይፋ ማጋራት መች ነው ስሜት የሚሰጠው፣ ግላዊ ቅንብርስ መች ነው ተመራጭ የሚሆነው?

እርስዎ በሚጠቀሙባቸው የማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርሞች ወይንም በነዚያ ፕላትፎርሞች ላይ በሚያስተዋውቁ ሶስተኛ ወገኖች ላይ መረጃዎ ማጋራት ምቾት ይሰጠዎታል? ለምን አደረጉ፣ ወይም ለምን አይሆንም?

ይህ ንግግር ስለ ግላዊነት ቅንብሮችዎ የተለየ ሀሳብ እንዲመጣልዎ አድርጎዎታል? ለምን አደረጉ፣ ወይም ለምን አይሆንም?

# ምድብ ሥራ

## ምድብ ሥራ

### ምድብ ስራ

አሁን ስለ ግላዊነት፣ ሰዎች ባጋራነው ይዘት ላይ ተመስርተው ምን ማጥራት እንደሚችሉ፣ የተለያዩ ሰዎች መልእክቶችን እንዴት በተለያየ መንገድ መረዳት እንደሚችሉ፣ ከሆነ ታዳሚ ጋር መጋራት የሚፈለጉዋቸው ነገሮችን ከመምረጥ ጋር በተያያዘ ቅንብሮች ለምን ጠቃሚ እንደሚሆኑ በተመለከተ ተነጋግረናል፣ አሁን የተማሩትን ነገር ተግባራዊ እናድርግ።

በሚቀጥሉት 30 ደቂቃዎች፣ እያንዳንዳቹ በግል፣ ስለሚከተሉት ሶስት ሁኔታዎች ሀሳብዎ ይስጡ እና ስለ እያንዳንዳቸው አጫጭር መልስ የያዙ አንቀጾን ይጻፉ:

1. ሲንአድ የአስራ ሶስት አመት ልጅ ስትሆን፣ ዳንስ መለማመድ ጀምራለች። እስካሁን ገና በጥሩ ሁኔታ እንዳልቻለቺው ይሰማታል፣ ይሁን እንጂ ለዳንስ ያላት ልዩ ስሜት ለጓደኞችዋ ለማጋራት እና የእነሱን ግብአት ለማግኘት ትሻለች። እስዋ በምትወዳቸው ዘፈኖች የጨፈረቻቸው ዳንሶች የሚያሳይ ቪድዮ በማህበራዊ ሚድያ ፕላትፎርም ለማጋራት እያሰበች ነው። ምን አይነት ፕላትፎርም እንድትጠቀም ይመክሩዋታል? የዛ ፕላትፎርም ምርጥ ግላዊነት ቅንብሮች ምን መሆን አለባቸው ብለው ያስባሉ? ለምን እንደሆነ ያብራሩ።
2. Reza የአስራ ስድስት አመት ልጅ ነው፣ ምግብ የማብሰል እና አዳዲስ የምግብ አሰራር አይነቶች የመፍጠር ልዩ ፍላጎት አለው። በጣም የሚደሰትባቸው ብዙ የደሮወጥ ምግቦችን ሰርቷል፣ እናም የሰራቸው ምግቦች ከጓደኞቹ እና ምግብ ማብሰል ላይ ፍላጎታ ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር መጋራት ይፈልጋል። ምን አይነት ፕላትፎርም እንድትጠቀም ይመክሩዋታል? የዛ ፕላትፎርም ምርጥ ግላዊነት ቅንብሮች ምን መሆን አለባቸው ብለው ያስባሉ? ለምን እንደሆነ ያብራሩ።
3. ኣልዋዚ የአስራ ስምንት አመት ልጅ ናት፣ በሚቀጥለው ወር ስራ መፈለግ ትሻለች። አሰሪዎች የስራ ማመልከቻዋ ማየት እንደሚፈልጉ ታውቃለች፣ ነገር ግን እንዴት ውጤታማ ማመልከቻ መጻፍ እንደምትችል እርግጠኛ አይደለችም። እስዋ አይቲ ዘርፍ ላይ ነው መሰማራት የምትፈልገው፣ ነገርግን ምን አይነት ስራ ማግኘት እንደምትችል እና ለስራዎቹ በቂ ብቃት እንዳላት አታውቅም። እስዋ ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ሌሎች ሰዎች ምክር እና ጥቆማዎችን ማግኘት ትሻለች፣ ነገርግን አሁን ከምታውቃቸው ሰዎች ውስጥ አንድም በአይቲ ዘርፍ የሚሰራ የላትም። ኣልዋዚ ምን አይነት ፕላትፎርም እንድትጠቀም ይመክሩዋታል? የዛ ፕላትፎርም ምርጥ ግላዊነት ቅንብሮች ምን መሆን አለባቸው ብለው ያስባሉ? ለምን እንደሆነ ያብራሩ።

የሚቻል ከሆነ፣ በሚቀጥለው እንደቡድን ሲሰባሰቡ፣ ተሳታፊዎችን በተመሳሳይ የቡድን አባላት ብዛት ያደራጁዋቸው እና እያንዳንዱ ቡድን በስራው ላይ የየራሱ ሀሳቦች እንዲያጋራ ያድርጉ።

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።